Monday, 06 April 2015 0

# መንግስትንና የዳያስፖራ ተቃዋሚዎችን ግራ ያጋባ ዘመን

"ሉዓላዊነት" በሚል ሰበብ፣ አገር ውስጥ "በዜጎች ላይ ያሻኝን ብፈፅም ማንም አያገባው" ብሎ መዝመት አስቸጋሪ ሆኗል "አሜሪካ፣ አውሮፓ ገብቻለሁ" ብሎ፣ በዘፈቀደ "የኤምባሲ አጥሮችን በመጣስ" ላይ ያተኮረ የተቃውሞ ስትራቴጂ አያዋጣም

እንግዳ ቁጥር 1

"በመንግስት የሰፈራ ዘመቻ ከእርሻ ማሳዬ ተፈናቅያለሁ" የሚሉ አንድ የጋምቤላ ገበሬ፤ ከአዲስ አበባው የአራት ኪሎ ቤተመንግስት እስከ ለንደኑ የዌስትሚንስተር ፓርላማ ድረስ፣ "ቁንጮ ፖለቲከኞችን የሚያጨቃጭቅ አሳሳቢ ጉዳይ ይሆናል" ብሎ ማን ጠበቀ? እንዴትስ የ 10 ቢሊዮን ብር ጥያቄ ሊሆን ይችላል? ለመንግስት፣ ፈፅሞ ያልተጠበቀ ትልቅ ፈተና እንደሚሆንበት አያጠራጥርም፤ "ዱብዳ" ነው። ለአንዳንድ ተቃዋሚዎች ደግሞ፣ ያልታሰበ ሲሳይ ነው፤ "በተዓምር የተገኘ መና"። በእውን እንዲከሰት ይቅርና በህልማችን እንዲመጣ ያልጠበቅነው ድንገተኛ ነገር ነው በማለት፤ እንደ "ዱብዳ" ወይም እንደ "ተዓምር" ቢቆጥሩት አይገርምም። ግን ለምን ድንገተኛ ሆነባቸው? ዘመኑን እለት በእለት እየተከታተሉ፤ ዓለምን ከዳር እስከ ዳር እየቃኙ፣ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሁኔታዎችን ለማናገናዝብ በቂ ጥረት አላደረጉም ማለት ነው።

እንግዳ ቁጥር 2

አሜሪካ ዋሺንግተን የሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ላይ ባነጣጠሩ የዳያስፖራ ተቃዋሚዎችና በኤምባሲው የፀጥታ ሰራተኞች መካከል አምባጓሮ የተፈጠረ ጊዜ ታስታውሳላችሁ? የፀጥታ ሰራተኛው የማስጠንቀቂያ ጥይት እንደተኮሰ፤ ተቃዋሚዎች ግቢውን ጥሰው በመግባት ባንዲራ እንዳወረዱ... ወዘተ የወቅቱ ትልቅ መነጋገሪያ ነበር። በዚሁ አላቆመም። በዋሺንግተንም ሆነ በአውሮፓ መዲናዎች፣ ተመሳሳይ ጀብዱ ለመፈፀም እንዳቀዱ የገለፁ አንዳንድ የዳያስፖራ ተቃዋሚዎች፣ "ሁነኛና አስተማማኝ የተቃውሞ ስትራቴጂ" የተገለጠላቸው ያህል ፈንጥዘዋል። ለብዙዎችም አሳማኝ ሆኖ ታይቷቸው ነበር። መንግስት በበኩሉ ከፍተኛ ስጋት እንዳደረበት፣ በወቅቱ ካወጣቸው መግለጫዎች መታዘብ ይቻላል።

እንደተጠበቀውም፣ በአሜሪካ እንደታየውን ክስተት ወዲያውኑ ለመድገም የወሰኑ የዳያስፖራ ተቃዋሚዎች፣ በስዊድን የኢትዮጵያ ኤምባሲን ጥሰው ለመግባት እንደሞከሩ ሲዘገብ ሰማን። ከዚያስ? ከዚያማ ኤምባሲ ጥሶ የመግባት ወሬ፣ እንደ ሰደድ እሳት ሲግለበለብ እንዳልሰነበተ ድንገት እልም ብሎ ጠፋ። ይሄውና ድምፁን ሳንሰማ ወራት ተቆጠሩ። ምን ተፈጠረ? ያ አንዳንድ የዳያስፖራ ተቃዋሚዎች የተዘመሩለትና መንግስት የሰጋበት፣ "የተቃውሞ ስትራቴጂ" ድንገት ኩምሽሽ ብሎ መጥፋቱ፤ ለተቃዋሚዎቹ "ዱብዳ"፣ ለመንግስት ደግሞ "ተዓምር" ሆኖ ሊታያቸው ይችላል። የዘመኑንና የአለምን ሁኔታ ባያገናዝቡ እንጂ፤ ነገሩ ድንገተኛ ባልሆነባቸው ነበር። እንዴት በሉ።

የኤምባሲው አምባጓሮ በተፈጠረበት ሰሞን፣ እዚያው ዋሺንግተን ውስጥ የአገሪቱን ፖለቲከኞች ዘንድ አሳሳቢ የነበሩ ሁለት ጉዳዮችን ብቻ ማስታወስ በቂ ይመስለኛል። አንደኛው፣ የፕሬዚዳንቱ ቤተመንግስትን ለአደጋ ያጋለጠ ድርጊት ነው - የኋይት ሃውስን አጥር ጥሶ የገባ ተጠርጣሪ፣ የፀጥታ ሰራተኞች፣ አነፍናፊ ውሾች፣ የጥበቃ መቆጣጠሪያ መሳሪያዎች ሳያግዱት፣ የፕሬዚዳንቱ ቢሮና መኖሪያ ቤት ወደሚገኝበት ህንፃ ገብቶ ከኮሪደር ኮሪደር ሲዟዟር እንደተያዘ በአገሪቱ የሚዲያ ተቋማት ሲዘገብ ምን የተፈጠረ ይመስላችኋል? የፖለቲካ ማዕበል።

ዋሺንግተን ቀውጢ ሆነች። ቀደም ሲል ሳይታወቁ የቆዩ ሌሎች የፀጥታ ጥበቃ ድክመቶች ከተደበቁበት እየፈለፈሉ የሚያወጡ ባለሙያዎችና ጋዜጠኞች፣ ነገሩን የዋዛ አላዩትም። የአገሪቱ ኮንግረስ (ፓርላማ) በበኩሉ፣ ባለስልጣናትንና ባለሙያዎችን እያስጠራ በጥያቄ ለማፋጠጥ ጊዜ አልፈጀበትም። የቤተመንግስት የፀጥታ ኤጀንሲ ዳሬክተር፣ በጥቂት ቀናት ውስጥ ከስልጣናቸው ተሰናበቱ። አሸባሪነት በገነነበት ዘመን፣ አጥር ተጥሶ የፀጥታ ሲፈጠር፣ እንደዋዛ አይታይም። በዚያ ላይ፣ በዋሺንግተን የኤምባሲዎችን ፀጥታ የመጠበቅ ሃላፊነት የማን ቢሆን ጥሩ ነው? የቤተመንግስት ፀጥታ ኤጀንሲ ነው፣ የኢንባሲዎችን ፀጥታ የሚቆጣጠረው። የኋይትሃውስ አጥር ተጥሶ፣ ከፍተኛ የፖለቲካ ቅሌት የወረደበት ይሄው ኤጀንሲ፤ እንደገና በየኤምባሲው ሌላ የፀጥታ አደጋ እንዲከሰት ፈቃደኛ የሚሆን ይመስላችኋል? የማይመስል ነገር!

ምን ይሄ ብቻ! ከኤምባሲ ጋር በተያያዘ፣ የአሜሪካ መንግስት ሌላ ተጨማሪ ራስ ምታት አለበት። ከ 30 ዓመታት በፊት በኢራን እና በሊባኖስ ምድር የአሜሪካ ኤምባሲዎች ላይ የደረሰውን ጥቃት ስለማይረሱት ብቻ አይደለም። ከዚያ በኋላም ኬንያና ታንዛኒያ ውስጥ ትልልቅ ጥፋቶችን አስተናግደዋል። ይሄ አልበቃ ብሎ፤ በሊቢያ የአሜሪካ አምባሳደርን ጨምሮ የበርካታ አሜሪካዊያንን ሕይወት የቀጠፈው ጥቃት፣ እንደ እሳት እያንገበገባቸው እንደሆነ ለመረዳት ከባድ አይደለም።

በኮንግረስና በፕሬዚዳንታዊ የምርጫ ዘመቻ ሳይቀር ላይ እንደ ትኩስ ጉዳይ ፖለቲከኞችን ዛሬ ድረስ ሲያጨቃጭቅ መስማት ትችላላችሁ!

**“Benghazi Attack”** ብለው የሰየሙትን ጥቃት፣ ኮንግረስ ውስጥ አራት ቋሚ ኮሚቴዎች ባለስልጣናትን፣ ምስክሮችንና ባለሙያዎችን እየጠሩ ለበርካታ ወራት በየፊናቸው ምርመራ ማካሄዳቸውንም አትርሱ። ይህም አልበቃም፤ ጉዳዩን የሚያጣራ ራሱን የቻለ ኮሚቴ እንዲቋቋም በኮንግረስ ስለተወሰነ፤ ይሄውና እስከዛሬ ምርመራው አለመቋረጡን ስትመለከቱ፤ ምን ያህል አክብደው እንደሚያዩት መገንዘብ ትችላላችሁ። ደግሞስ፣ በሊቢያ፣ በግብፅ፣ በቱኒዚያ እና በበርካታ አገራት ውስጥ፣ ለአሜሪካ መንግስት የኤምባሲዎች የፀጥታ ጥበቃ፣ እረፍት የማይሰጥ ስጋት እንደሆነ አናውቅም እንዴ? ለአውሮፓ መንግስታትም እንዲሁ ያሳስባቸዋል። ምናለፋችሁ? የአሜሪካና የአውሮፓ መንግስታት፣ ኤምባሲዎቻቸውን የፀጥታ ጥበቃ የሚነካ ነገር በቸልታ ወይም በዋዛ እንዲታለፍ አይፈልጉም። በዋና ከተሞቻቸው ውስጥ የሚገኙ የሌሎች አገራት ኤምባሲዎችም ላይ፣ ምንም አይነት ስጋት እንዲፈጠር አይፈቅዱም።

ምን ለማለት ፈልጌ ነው? ይህንን የዘመናችንና የአለምን ሁኔታ የሚያገናዝብ ሰው፤ “ኤምባሲዎች ላይ ያነጣጠረ የተቃውሞ ስትራቴጂ” ከአንድሰሞን ሆይሆይታ በኋላ፣ ድምፁ እልም ብሎ ቢጠፋ፤ “ዱብዳ” ወይም “ተዓምር” ሆኖ አይታየውም ለማለት ነው።

ወደ ደቡብ አፍሪካ ቪዛ አስመታለሁ በማለት ሰዎችን አጭበርብረዋል ተብለው የተከሰሱ፣ የባሌስትራ ቁርጥራጭ ወርቅ ነው ብለው ብሔራዊ ባንክን አታልለዋል ተብለው የተከሰሱ፣ ሚስታቸውን ደብድበው ገድለዋል ተብለው የሚፈለጉ ሦስት ተጠርጣሪዎች፣ ከደቡብ ሱዳን፣ ከአረብ አገር እና ከጀርመን ተይዘው እንደመጡ ታውቃላችሁ።

ቀደም ብዬ ያነሳሁት የእርዳታ ጉዳይም፣ ከበድ ያለ ጉዳይ ነው። ብዙዎች ከባድነቱን ለማመን ይቸገሩ ይሆናል። ነገር ግን፣ የጋምቤላው ገበሬ፣ “ከእርሻ ማሳዬ በመንግስት የሰፈራ ዘመቻ ተፈናቅያለሁ፤ የእንግሊዝ መንግስት ለሰፈራ ዘመቻው እርዳታ በመስጠት ስለተሳተፈ ይጠየቅልን” በማለት በለንደን ያቀረቡት ክስ የዋዛ አይደለም። በስደት ኬንያ የሚገኙት እኚሁ ገበሬ በጠበቃቸው ባቀረቡት ክስ፣ የካሳ ክፍያ ቢጠይቁም፣ ጉዳዩ በዚህ ብቻ አላበቃም። እንግሊዝ ለኢትዮጵያ መንግስት የሚሰጠው እርዳታ፣ ከላይ እስከ ታች ተመርምሮ መጣራት እንደሚኖርበት ፍ/ቤቱ ተናግሯል። እርዳታው ቀላል እንዳይመስላችሁ። ከአሜሪካ በመቀጠል፣ ለኢትዮጵያ ዋነኛዋ እርዳታ ሰጪ የሆነችው እንግሊዝ፣ በየአመቱ ወደ **10** ቢሊዮን ብር የሚጠጋ እርዳታ ትለግሳለች። በአንድ ገበሬ ክስ የተነሳ፣ የሃያሏ አገር መንግስት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲውን እንዲመረምር የፍርድ ቤት ጫና ሲመጣበት አስቡ። ከዚሁ ክስ ጋር ተያይዞ፣ የኢትዮጵያ መንግስት በየአመቱ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬና እርዳታ የሚኛገኝበት ትልቅ ምንጭ ስጋት ላይ ሲወድቅ ይታያችሁ።

አስቸጋሪ ነው። መንግስት እንደዘወትሩ፤ “ይሄ የኒዮሊበራሎች ዘመቻ ነው” በማለት ለመከራከር ቢያስብ እንኳ፣ አመቺ አይደለም። ሶሻሊስቶች፣ አሜሪካንና እንግሊዝን ለማንቋሸሽ በሚዘወትሩት የፕሮፓጋንዳ ስልት፣ “የኒዮሊበራሎች ሴራ ነው” የሚል አባባል እያስተጋባ፣ አንድ ተራ ገበሬ ያቀረቡትን ክስ ለመከላከል ቢሞክር ትዝብት ላይ ከመውደቅ ያለፈ ውጤት አያገኝም። ይሄኛው የፕሮፓጋንዳ ስልት አላዋጣ ሲል፤ በአገራችን ባህል እንደተለመደው፣ “ይሄ የአንድ ግለሰብ ጉዳይ ነው” በማለት መንግስት ነገሩን ለማጣጣልና ለማስተባበል ቢሞክርስ? ይሄም አያዋጣውም። እንዲያውም በተቃራኒው፤ “እንዲህ አይነት ማስተባበያ፣ የመንግስትን ጥፋተኝነት ከማረጋገጥ አልፎ፣ ሰዎች ላይ ለሚደርስ ጉዳት ደንታ ቢስ መሆኑንም ያሳያል” የሚል ምላሽ ነው የሚያጋጥመው። የእያንዳንዱ ሰው መብት መከበር አለበት የሚለው መሰረታዊ የነፃነት አስተሳሰብ፣ በአሜሪካና በአውሮፓ አሁንም ድረስ ጠንካራ ነዋ።

በተቃራኒው፣ የእንግሊዝ መንግስትን ምላሽ ተመልከቱ - “ለሰፈራ ዘመቻ እርዳታ አንሰጥም። ለኢትዮጵያ መንግስት የምንሰጠውን የእርዳታ ትብብር፣ በየጊዜው እንመረምረዋለን። ወደፊትም እንመረምረዋለን። ውጤታማ ያልሆኑትን እየሰረዝን፣ ውጤታማ የትብብር መስኮችን በማጠናከር ነው የምንሰራው” ብሏል የእንግሊዝ መንግስት። እንግዲህ፤ በርካታ ነገሮች እንደድሮ ስላልሆኑ፤ የአገራችን መንግስት የዘመናችንንና የዓለምን ሁኔታ በማገናዘብ፣ የእንግሊዝን አይነት ምክንያታዊ አካሄድ ከወዲሁ ቢለማመድ አይሻለውም ትላላችሁ?

በሚዲያ ነፃነት ዙሪያም፣ ከዘመኑ ጋር ለመራመድ፣ ገና ሊለማመዳቸው የሚገቡ ቁምነገሮች አሉ። የቴሌቪዥን ጣቢያ ስርጭትን ለብቻው በሞኖፖል የያዘው የአገራችን መንግስት፤ በርካታ ሬድዮ ጣቢያዎችን እየተቆጣጠረና አዳዲስ ጣብያዎችን እየገነባ ቢሆንም፣ ለሁለት ለሦስት የግል የኤፍኤም ሬድዮ ጣቢያዎች ፈቃድ መስጠቱ በጎ ጅምር ነበር። በእርግጥ፣ ከ **15** አመት በፊት የወጣው የብሮድካስት አዋጅ ላይ፣ ለሬዲዮ ብቻ ሳይሆን ለቴሌቪዢንም ጭምር፣ የግል የስርጭት ጣቢያ

ለማቋቋም የሚያስችል ፈቃድ እንደሚሰጥ ይደነግጋል። ግን ተግባራዊ አልሆነም። ወደፊትም ተግባራዊ አይሆንም ተብሏል። የማሰራጫ ጣቢያ ማቋቋም የሚችለው መንግስት ብቻ እንደሚሆንና፣ ለግል ድርጅቶች ቻናል እንደሚያከራይ የሚገልፅ አዲስ ረቂቅ ህግ ተዘጋጅቷል። እስቲ አስቡት። በዛሬው የቴክኖሎጂ ዘመን፣ እንደ ድሮው መንግስት ሁሉንም ነገር በሞኖፖል ተቆጣጥሮ ሊቀጥል ይፈልጋል? ለነገሩ፣ ከሬድዮና ከቴሌቪዢን በተጨማሪ፣ የጋዜጣ ስርጭትንም ካልተቆጣጠርኩ ብሎ አዲስ ህግ ወይም መመሪያ እንደሚያዘጋጅ ሲገልፅ ከርሞ የለ!

እንዴት ነው ነገሩ? ብዙ ነገሮች እንደድሯቸው እንዳልሆኑና ብዙ ነገሮች እንደተቀየሩ አልገባውም ማለት ነው? በመላ አገሪቱ በየቀኑ የሚሰራጨው የግል ጋዜጣና መፅሔት ስንት ቢሆን ነው? ምናልባት 10 ሺ? እና የእነዚህን ጋዜጦች ስርጭት ለመቆጣጠር ይፈልጋል።

እስቲ ሁላችሁም፣ የመንግስት ሃላፊዎችም ጭምር፣ የየራሳችሁን ግቢ እና ጎረቤቶቻችሁን ይመልከቱ። ምን ይታያችኋል? የሳተላይት ቴሌቪዥን ዲሽ! ዲሽ የተከሉ ሳይሆን ያልተከሉ መቁጠር ይሻላል። ከግቢ ወጣ ብለው የየሰፈራቸውን ግራና ቀኝ ሲቃኙስ፣ በየጣሪያው ወደ ሰማይ ያንጋጠጡ ዲሾች አካባቢውን እንዳጥለቀለቁት አያዩም? ለዚያውም በትላልቅ ብቻ ሳይሆን በትናንሽ ከተሞችም ጭምር ነው። ይህ ብቻ አይደለም።

የቅርብ ጊዜ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ወደ ሁለት ሚሊዮን የሚጠጉ ኢትዮጵያውያን ኢንተርኔትን ይጠቀማሉ። አንዳንዱ ሰሞነኛ የሆሊውድ ፊልሞችንና እለት በእለት በአሜሪካ የሚሰራጩ ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማዎችን በትኩሱ ከኢንተርኔት እየሸመጠጡ ይኮመኩማሉ። አዳዲስ ሙዚቃዎችን ያፍሳሉ። አንዳንዱ ደግሞ፣ ዘመን የማይሽራቸው ትልልቅ መፃህፍትን በገፍ ያካብታል። ወይም በየእለቱና በየሳምንቱ እየታተሙ በአለም ገበያ ቁንጮውን ቦታ የሚይዙ መፃህፍትን ከኢንተርኔት እየበረበረ ያከማቻል። አንዳንዶቹ ብልጦች፣ ለሙያቸው የሚጠቅሙ መጻሕፍትን፣ ጥናቶችንና የስልጠና ቪዲዮዎችን ይሰበስባሉ። በእርግጥ፣ እንዲህ አይነት የኢንተርኔት ተጠቃሚ ኢትዮጵያዊያን ሲደማመሩ፣ በቁጥር ጥቂት ሊሆኑ ይችላሉ። አብዛኛው ተጠቃሚስ?መጀመሪያ ላይ በዲቪ ሎተሪ አነሳሽነት ነው ብዙ ሰው የኢሜይ ደንበኛ የሆነው። ቀጥሎም በስካይፒ እና በዩቱብ። ከዚማ ፌስቡክ እና ረቀቅ ያሉ ሞባይሎች መጡና አዳሜ ወደ ኢንተርኔት ሰተት ብሎ እንዲገባ ሰበብ ሆኑለት። ዛሬ፤ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን፣ ኢንተርኔት ከዘወትር ሕይወታቸው ጋር እያዋሃዱት ነው። በየፊናቸው፣ ከመቶ ሺ እስከ ዘጠኝ መቶ ሺ የሚደርሱ ተከታታይ ደንበኞችን ለማፍራት የቻሉ በርካታ ዌብሳይቶችና የፌስቡክ ገፆች እንደተፈጠሩ ብቻ ማየት በቂ ይመስለኛል።

እንዲያም ሆኖ፣ መንግስት ዛሬም በጣት የሚቆጠሩት ጋዜጦችና መፅሔቶችን በአይነቁራኛ ከማየትና ሙሉ ለሙሉ ለመቆጣጣር ከመጣጣር አልተቆጠበም። ዘመኑ የኢንተርኔት እንደሆነ ጠፍቶት ነው? ወይስ፣ ኢንተርኔትን መቆጣጠር፣ ጋዜጣና መፅሔትን እንደመቆጣጠር ቀላል ስላልሆነ? በእርግጥ አንዳንድ ዌብሳይቶች ኢትዮጵያ ውስጥ በቀላሉ እንዳይታዩ መሰናከልና አጥር መዘርጋት አይከብድም። ነገር ግን፣ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የፌስቡክ ደንበኞች ዘንድ የሚደርሱ መረጃዎችን፣ ፅሁፎችን፣ ምስሎችንና ቪዲዮዎችን ለመቆጣጠር መሞከር ግን አስቸጋሪ ነው። ብዙ ገንዘብና ብዙ ጊዜ ማባከን ነው ትርፉ። እንደ ቻይና እንኳ መሆን አይቻልም። እንደ ሰሜን ኮሪያ አገሬውን ከአለም ነጥሎ በመቆለፍ አፍኖ መያዝም አያዛልቅም። ለጊዜው የአገራችን መንግስት በኢንተርኔት አለም ውስጥ ብዙም የአፈና አማራጮች የሉትም። ያው፤ የልማድ ነገር ሆኖ፣ የፈረደባቸው የግል ጋዜጦችና መፅሔቶችን ማስጨነቁን ግን አያቋርጥም - ትርጉም የለሽ ቢሆንም። ውጤት ለሌለው ነገር ጊዜውንና ገንዘቡን ያባክናል። ከዚህ ይልቅ፤ ለስልጡን የሚዲያ ነፃነት ቢጣጣርና ቢለማመድ አይሻለውም?

ነገሮች እንደድሮ አይደሉም።

አዲስ አድማስ